# የአዜብ መስፍን ህልም !

የመሪያችን ባለቤት ወይዘሮ አዜብ አያድርግባቸውና በህልማቸው ሞተው መንግስተ ሰማያት ሲገቡ ያያሉ ። እንደገቡም ቅዱስ ጴጥሮስ በክብር ይቀበላቸውና መንግስተ ሰማያትን እያዟዟረ ያስጎበኛቸዋል። ታዲያ በጉብኝታቸውም ወቅት እጅግ በጣም በርካታ የግድግዳ ሰአት በየቦታውና በየግድግዳው ተሰቅሎ በማየታቸው ይገረሙና ቅዱስ ጴጥሮስን እንዲህ ሲሉ ይጠይቁታል።

"ለመሆኑ ይሄ ሁሉ ሰአት ምን ያደርጋል ብላችሁ ነው? "

ቅዱስ ጴጥሮስም "ይሄ እያንዳንዱ ሰአት በምድር የሚገኘውን እያንዳንዱን ሰው የሚወክል ነው ። ጥቅሙም ውሸትን ለመቆጣጠር ነው። " ብሎ ይመልሳል

ወይዘሮ አዜብም ደንገጥ ብለው "እንዴት ነው ውሸትን በሰአት የምትቆጣጠሩት? " ብለው ይጠይቃሉ።

ቅዱስ ጴጥሮስም ሲመልስ "በምድር የሚገኘው እያንዳንዱ ሰው አንዴ በዋሸ ቁጥር ሰአቱ አንድ ዙር ይዞራል ደግሞም ሲዋሽ እንደዛው ይቀጥላል "። በማለት ከገለጸላቸው በኋላ፤ ለምሳሌ ይልና ግርግዳው ላይ ካሉት አንዱን የማይነቃነቅ ሰአት እያመለከተ "ይህ ሰአት የማዘር ትሬዛ ሰአት ነው። ማዘር ትሬዛ በህይወት ዘመኗ ዋሽታ ስለማታውቅ ሰአቱ አንዴም ዞሮ አያቅም። " በማለት ሲገልጽላት

ወይዘሮ አዜብ በአንደኛው ግድግዳ ላይ ያሉትን ሳይቆሙ የሚሽከረከሩ ሰአቶች አይታ "እነኝህስ የውሸታም ሰዎች መሆናቸው ነው? " ብላ ትጠይቃለች

ቅዱስ ጴጥሮስም "አዎ በዚህ መደዳ ያሉት በሙሉ የፖለቲካ ሰዎች ሰአት ናቸው። ለምሳሌ ይሄ የክሊንተን ፥ ይሄ የጎርባቾቭ፥ ይሄ የብሌር፥ " እያለ ያሳያት ጀመር።

ወይዘሮ አዜብ የባለቤቷም ሰአት እዚሁ አካባቢ እንደሆነ በመገመት ለማየት ጓጉታ "የኔስ ባለቤት ሰአት የቱ ነው "ብላ ትጠይቃለች።

ቅዱስ ጴጥሮስም ሲመልስ "ያንቺ ባለቤት ሰአት አፐስቴር ጌታ ቢሮ ውስጥ እንደ አየር ማቀዝቀዣ **(fan)** እየተጠቀመበት ነው" ብሏት እርፍ። የባለቤትዋ ሰአት እንደ ፋን ሲሽከረከር ታይትዋት ነው መሰለኝ ወይዘሮ አዜብም በድንገት ጉብኝትዋን አቋርጣ ከእንቅልፏም ባና ከኤዶም ገነት የከነፈች አራት ኪሎው ገነት ቤተመንግስት ከች አለች እላችኋለሁ።

ከፉ እልም በሉ